# የአልኮል እና ሌሎች እፃች (ድራጎች) አለአግባብ መጠቀም፤ ደንቦች

## I. መግቢያ

ተማሪዋችን አለአግባብ ድራግ የመጠቀም ችግር መርዳትን በተመለከተ ዋነኛው ኋላፊነት ያለው በተማሪዋችና በወላጆች ላይ ነው። ሆኖም የትምህርት ቤት ቦርዱ ድራጎችን አለአግባብ የሚጠቀሙ ተማሪዋች ድጋፍ ለመስጠት የትምህርት ቤት ምቹ ከባቢ ኢንቫይሮሜንት በመፍጥር ዘርፈ-ብዙ የድጋፍ ስርዓት(MTSS) የመፍትሄ አቅጣጫ ይከተላል። በመሆኑም የትምህርት ቤት ቦርዱ የእፅ እጠቃቀም መከላከል እና ቅድሚያ ጣልቃ የመግባት ፕሮግራሞች እንደ የሰው ፍላጎት የሚለያይ እንዲዘጋጅ ያግዛል። በዚህ ከተካተቱት ፕሮግራሞች መካከል ተማሪዋችን የህገወጥ እፆች እና ህጋዊ ድራጎችን አለአግባብ መጠቀም ጎጂነት ማስተማር፣ እና እፅ አለአግባብ መጠቀም እንዴት መለየት እንደሚችሉ በሚመለከት እንዲሁም ፕሮግራም እና እንቅስቃሴዋችን የጣልቃ ገብነት በሚመለከት ፕሮግራም ማዘጋጀት በትምርህት ቤት አስተዳደር ዲቪዝን እፅ አለአግባብ መጠቀም የመከላከልና እና አስቀድሞ ጣልቃ የመግባት ፕሮግራም በቡድን በመሳተፍ፣ እና በግል ምክር እና በሌላ ፕሮግራም በማግኘት ሊሰጥ ይችላል። በተጨማሪም ተማሪዋችና ወላጆችን ወደ ማህበረሰባዊ ተቋማት በመላክ ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ በወላጅ ወጪ የሚሸፈን ሊደረግ ይችላል።

## II. አላማ

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የመዋእለ ህጻናት-12 የአደንዛዝ እፅ መከላከል እና የቅድሚያ ጣልቃ መግባት አገልግሎቶች የሚያገለግለው ተማሪዋች በተለይ ያለባቸውን የእፅ አለአግባብ የመጠቀም ችግር ለማስቀረት ከዚህ ጋር ተያይዘው ከትምህርት አቀባል ችግር ጋር በተገናኘ የሚፈጥሩ እንቅፋቶች (ይህም፣ እፅ መጠቀም፣ በተሳሳተ መልክ ወይም አለአግባብ መጠቀም) እና በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አገልግሎት አሰጣጥ ድርሻ ውስጥ ይካተታል። ይህ ደንብ፤

- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ድራግ በትምህርት ቤት ፖሊሲ ይዘረዝራል፣ እንዲሁም
- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የድራግ አለአግባባ የመጠቀም እና ጣልቃ የመግባትን አሰራር እንቅስቃሴ ዘዴዋችና መመሪያዋች ይዘረዝራል።

## III. ትርጓሜዋች

A. **የአልኮል እና ሌሎች ድራጎች ደንብ መተላለፍ፤**

1. <u>አንድ ተማሪ</u> አልኮል፣ ሲጋራ እና/ወይም የሲጋር ምርቶች ወይም ሌሎች ድራግ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ አውቶብስ ወይም ትምህርት እንቅስቃሴዋች ወቅት ከትምህርት ቤት ንብረት ውስጥ ሆነ ውጭ መጠቀም የለበትም። ይህም የሚያከትተው ሆኖም በዚህ አይወሰንም ጭስ አልባ ሲጋራ፣ ኢ-ሲጋራ፣አናቦሊክ ስቴሮይድ፣ ድራግ የሚመስሉ፣ ፖራፐርናሊያ ድራግ እና ማንኛውም በዶክተር ትእዛዝ ወይም ከትእዛዝ ውጭ የሚገዙ ድራጎች በፖሊሲ JHCD መመሪያ መሰረት በአግባብ ያልተያዙ ወይም በጥቅም ላይ ያልዋሉ።

2. <u>አንድ ተማሪ ማድረግ አይኖርበትም፤</u>
   - እፅ መያዝ፣ መግዛት፣ ወይም ለመያዝ፣ ለመግዛት መሞከር የለበትም፣
   - በተፅእኖ ስር መሆን የለበትም (ሕጋዊ የሆነ የመድሀኒት አጠቃቀም አይጠየቀም)፣
   - መጠቀም ወይም መገልገል ወይም ለመጠቀም ወይም ለመገልገል መሞከር።

   በደንቡ የተዘረዘሩትን ማንኛውንም የተከለከሉ እፃች (ወይም በተማሪው የቀረቡ/ለተማሪው የቀረቡ የተከለከሉ እፃች በደንቡ የተዘረዘሩ ወይም በደንቡ የተዘረዘሩ የተከለከሉ እፃች እንደሆኑ ተማሪው ያመነበትን።

B. **የድራግና ቁጥጥር ያለባቸው ነገሮች፤** የሚያጠቃልለው የአልኮል መጠጥ፣ ናርኮቲክ ድረግ፣ ሲጋራ ወይም የሲጋራ ምርቶች፣ ሃሊሲጅን ፣ አነቃቂ እፃች፣ ማደንዘዣ (ዲፕሬሰንት) ፣ ሌላ ማንኛውም በድራግ ቁጥጥር ህግ የተሸፈነ ነገር እንዲሁም የሚፈነዳ/ተቀጣጣይ የሚዋጥ ነገሮች እና/ወይም ኤሮሶል፣ ኢ-ሲጋራ (የኤሌክትሮኒክስ-እና

ኤሌክትሮኒክስ ያልሆኑ ማሳሪያዎች፣ መገልገያዎች፣ እቃዎች ለመሳብ እና ለማጨስ እና ለማንቦቅቦቅ የሚያገለግሉ) ፣አናቦሊክ ስትሮይድ፣ ሁለቱም በዶክተር ትእዛዝ ወይም ከትእዛዝ ውጭ የሚገዙ ድራጎች/ቁጥጥር የማይደረግባቸው ድራጎች በፖሊሲ JHCD እና ደንብ JHCD-R በመከተል የማይፈፀሙ ከሆነ እና ማንኛውም በተማሪ የተከለከሉ ነገሮች እንደሆኑ የቀረቡ ወይም ተማሪው የተከለከሉ እፆች እንደሆኑ ያመነባቸው ነገሮች።

C. **ፐራፐርናሊያ፤** የሚያካትተው መሳሪያ ፣ መገልገያ ፣ እቃዎች በመገልገያነት ወይም በመሳሪያነት ወይም በአንድ ላይ ተቀናጅቶ ህገወጥ እፅ ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ለማዋል ለመጠቀም የሚያገለግል። በተለምዶ ከሕግ ውጭ ድራግ አጠቃቀም ጋር የተገናኘ እና ቁጥጥር የሚደረባቸውን ድራግ የሚሰራጭባቸውን እቃዎችን ያካትታል።

D. **ዘርፈ-ብዙ የድጋፎች ሥርዓት(MTSS)፤** የችግር መፍቻ መንገድ ሞዴል ሁሉም ተማሪዎች ፍላጎት ለመመልከት የረዝም ጊዜ የአካዳሚ ውድቀት እንዳይከተል ቅድሚያ የመፍትሄ ጣልቃ ገብነት ለማድረግ የሚያስችል። በርካታ ደረጃዎችን የሁሉንም ተማሪዎች የአካዳሚ እና የባህሪ ውጤታማነት ለማሳደግ ትምህርትና ድጋፍ የመስጠት ሂደት የያዘ ነው ። የአንድ ተማሪ ውጤት ለውጥ ክትትል በመደበኛነት ኤም.ቲ.ኤስ.ኤስ(MTSS) ቡድን ይደረጋል እና ውጤቱም በቀጣይነት ለትምህርት እና ጣልቃ ገብነት ለማድረግ አገልግሎት ላይ ይውላል።

አንድ የድራግ አለአግባብ መጠቀም ሁኔታ ለመመልከት ዘርፈ-ብዙ የድጋፎች ሥርዓት የቅድሚያ ጣልቃ ገብነት መለያ፣ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ፣ እና በማስረጃ የተደገፈ አሰራር በተገቢው መጠን እና የጊዜ ገደብ በስራ ማዋል። ደረጃ 1፤ አጠቃላይ ዩነቨርሳል መከላከል፣ ደረጃ 2፤ የተመረጠ መከላከል/ ጣልቃ ገብነት፣ ደረጃ 3፤ ያነጣጠረ ጣልቃ ገብነት

E. **መልሶ-መግባት፤** የባህሪ ደንብ መጣስ ጋር በተገናኘ ከትምህርት ቤት ውጭ እገዳ ወይም ከት/ቤት ውጭ የህክምና ፕሮግራም ወደ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የሚመለሱ ተማሪዎች።

F. **የእፅ አለአግባብ አጠቃቀም የመከላከል እና ጣልቃ የመግባት አማካሪ (ኤስ.ኤ.ሲ-SAC)፤** የሚያመልከተው የምስክር ወረቀት ያለው የእፅ አለአግባብ አጠቃቀም አማካሪ የመከላከል ተግባራትን የምክር አገልግሎት እና የእፅ አጠቃቀም ችግር በተመለከተ ቅድሚያ ጣልቃ መግባት ነው። የእፅ አለአግባብ አጠቃቀም መከላከል እና ጣልቃ የመግባት አማካሪ(ኤስ.ኤ.ሲ) የሕክምና አገልግሎት አይሰጥም። ነገር ግን የእፅ አጠቃቀም ችግር የመለየት ስራ ፣ የመገምገም ስራ እና ትምህርት እና ሊሰጥ የሚችል የህክምና አገልግሎት በተመለከተ ምክር መስጠት እና በውጭ ወደሚገኙ አጋሮች የመላክ ስራ ያከናውናል። ኤስ.ኤ.ሲ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የድራግ አጠቃቀም መከላከል እና ቅድሚያ ጣልቃ መግባት ፕሮግራምን ይመራል።

## IV. የእፅ አለግባ መጠቀም መከላከል አገልግሎት ማግኘት፤

A. **አሰራሮች**

- በፌደራል፣ ስቴት ወይም በአካባቢ ባሉ ህጎች እና አሰራሮች ጋር በሚስማማ መልኩ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎች የባህሪ ደንብ የአልኮልና ህገወጥ ድራግ መጠቀም እና ያለአግባብ መጠቀም የተከለከለ ነው።
- ከአደንዛዥ እፅ ጋር በተያያዘ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎች የባህሪ ህግ በመጣስ በአልኮል እና ሌሎች ድራጎች (AOD) እንደወሰደ የተጠረጠረን ማንኛውንም ተማሪ ለሚመለከተው ርእሰ መምህር ወይም ተወካዩ ማንኛውም ሰራተኛ ሪፖርት ማድረግ አለበት።
- አግባብነት ያለው ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ የሚከተለው ቅጣት እና ወደ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የመዋአለ ህጻት-12 ያአግባብ ድራግ መጠቀም የመከላከል እና የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም መላካን ይወስናል።
- በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎች አገልግሎቶች ዲፓርትሜንት ውስጥ ያለ የመዋአለ ህጻት-12 ያለአግባብ ድራግ መጠቀም(SA) መከላከል እና የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም ነው። የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችና እና የተማሪ ድጋፍ ሰጪ ቡድን (ኤስ.ኤስ.ቲ. - SST) አባለት ናቸው ተማሪዎችን ወደ ያአግባብ ድራግ መጠቀም(SA) መከላከል እና የጣልቃ ገብነት ፕሮግራም አገልግሎት መላክ የሚችሉት። ሚስጢራዊነትን እና የግል መረጃ አሰራርን ተከትሎ በዚህ ሰነድ በሚስጢራዊነት አጠባበቅ ክፍል (VI.) ተዘርዝሮል። የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ.

ኤስ.ኤስ.ቲ (SST) አባላት ቢያንስ መያዝ የሚኖርበት የትምህርት ቤቱ ነርስ፣ የትምህርት ቤት ማህበራዊ ጉዳይ ሰራተኛ፣ እንዲሁም የተማሪው አማካሪዎችን ።

- የተማሪዋችን ባህሪ ደንብ የተላለፉ ተማሪዎች ከድራግ አጠቃቀም ወይም ማሰራጨት ጋር በተገናኘ ወደ አለአግባብ ድራግ መጠቀም የመለየት ወይም ግምገማ እንዲካሄ ይልካሉ ምን አይነት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ለመወሰን።
- ወላጆች ወይም ህጋዊ አሳዳጊዋች መፈረም አለባቸው በሰነዶች ሚስጢራዊነት ማስጠበቅን በተመለከተ ምርመራው ከመጀመሩ በፊት።
- ከምርመራው የሚገኘው ውጤት ለተማሪው፣ ለወላጅ/አሳዳጊ፤ እና በወላጅ/አሳዳጊ ፈቃድ የትምህርት ቤቱ ሪፈር ለሚደረግበት አካል ይላካል።
- በምርመራው የሚገኘው ውጤት በኤስ.ኤስ.ቲ  አባላት ውይይት ይደረግበታል (የሚስጢራዊነትና የግል ታሪክ የማስከበር ህጎችን በመከተል) ያም የተማሪውን የአካዳሚ ፣ የአእምሮ ጤና እና ያአለአግባብ የመጠቀም ፍላጎት የሚመለከት የአገልግሎት አሰጣጥ እቅድ መነሻ ይሆናል።
- ወላጅችና / አሳዳጊዋች፤ ወይም ተማሪው የሚሰጠውን የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ አገልግሎት የማይቀበሉ ከሆነ  ከተፈላጊው አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት የወላጆችና / አሳዳጊዋች ሃላፊነት ይሆናል።
- የተማሪው ፍላጎቶች ከድራግ ትምህርት በላይ ከሆነ ወደ ህክምና ለመላክ ወይም ከፍ ወደ አለ አገልግሎት ለማግኘት ከወላጅ/አሳዳጊ  እና ከተማሪው ጋር በመነጋገር መወሰን ይኖርበታል። ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ  ያለአግባብ ድራግ የመጠቀም ህክምና አይሰጥም።  በመሆኑም ተማሪው እርሱ/እርሷ ለሚፈልገው /ለምትፈልገው አገልግሎት የማገናኘት ሃላፊነት  የወላጆችና / አሳዳጊዋች  ይሆናል።  የወላጆችና / አሳዳጊዋች ሃላፊነት ማገናኘት ስራ ማከናወን ካልቻሉ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ ከልጆች ጥብቃ አገልግሎት(CPS) ጋር ይገናኛል።

B. **ደረጃ 1 - መከላከል/ትምህርት**

<u>የመከላከል ዘመቻ እና ወርክሾፐ</u> ፤  ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በመላ ትምህርት ቤት የማስገዘብ ዘመቻ በውስጥ እና በውጭ ያሉ ሪሶዋርሶችን በመጠቀም ይካሄዳል። አንዳንድ ዘመቻዋች ከውጭ አጋዢዋች ጋር በመተባበር ይካሄዳሉ። ለምሳሌ ፣ እፅ አለአግባብ የመጠቀም መከላከል ፕሮግራሞች ተከታታይ የሆኑ ወርክሾፖችን ለተማሪዋች እውቀት እንዲኖረቸው አስቸጋሪ ባህሪን እና አመለካከትን ለመከላከል በማስረጃ ላይ የተመረተ ሥርዓተ ትምህርት ማዘጋጀት።

<u>የትምህርት ደረጃ መመዘኛ (SOL)</u>፤ በትምህርት ደረጃ መመዘኛ ውስጥ  በጤና እና የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ሥርዓተትምህርት ውስጥ እፅ አለአግባብ የመጠቀም ትምህርት ተካቶል።  ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ የመዋእለ ህጻናት-12 ክፍል አለአግባብ የመጠቀም እና ቅድሚያ ጣልቃ መግባት ድጋፍ ሰጪ አስተማሪዋች በድራግ ትምህርት ይዘት በማማከርና የቴክኒክ ድጋፍ በመስትት ከጤና እና የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ዲፓርትሜንት ጋር በመተባበር በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን የትምህርት ይዘት ከትምህርት ደረጃ መመዘኛ (SOL) አላማ ጋር የድራግ ትምህርት ጋር በተቀናጀ መልኩ እንዲካሄድ ድጋፍ ያደርጋሉ።

<u>ትብብሮች፤</u> ድራግ ያለ አለ አግባብ የመጠቀምን  የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ ትምህርት ለመደገፍ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ ቅንጅትን እና ትብብር ማሳደግን ዋጋ ይሰጣል። ትብብር መፍጠር ከውስጥ እና ከውጭ አካላት ጋር እንደ የአሌክሳንደሪያ አለአግባብ ድራግ የመጠቀም መከላከል ህብረት (SAPCA) በጣም አስፈላጊ ነው በአግባቡ የድራግ መከላከልን እና የጣልቃ መግባት ፕሮግራሞችን ውጤታማ ለማድረግ። አጋዥ የሆኑት በቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ፣ በማማከር ፣ፋይናንስ በመስጠት እና በሌላም ያግዛሉ።  አስረጂዋችን እና ቀሳቁስችን በማቅረብ የሚጠይቀውን ዋጋ በመቀነስ እና ለተማሪዋች የሚቀርበውን ጥራት ያለውን የመከላከል አገልግሎት እና በቅድሚያ ጣልቃ መግባት ፕሮግራሞች በመጨመር  በጣም አስፈላጊ ናቸው።  በተጨማሪም የእነሱ ሙያ እና ተሳትፎ ለተማሪዎች የሚሰጠውን ፕሮግራም ያሰፋል።

C. ***ደረጃ 2፣ 3- ጣልቃ መግባት / መለየት***

1. <u>መለየት እና ግምገማ ፤</u> ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የመለየት እና የግምገማ ስራ ይሰጣል የሚከተለውን በማሰብ፤
   - ተማሪው መለስተኛ(MILD) ዝቅተኛ (አነስተኛ አደጋ )፣ አማካኝ(MODERATE) (መካከለኛ አደጋ) ወይም የከፋ(SEVERE) (ከፍተኛ አደጋ) የሆነ የእፅ አጠቃቀም ምልክቶች መሆኑን መወሰን፡፡
   - ተማሪው ሙሉ የሆነ አለአግባብ እፅ የመጠቀም ችግር እንዳለው መወሰን፡፡
   - የተማሪውን ፍላጎት የሚያሟላ ተገቢ የሆነውን አገልግሎት ሃሳብ ለወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተማሪዎች ማቅረብ፡፡
   - ኤስ.ኤስ.ቲ. አባላትን እና አስተማሪዎችን ተማሪውን እንዴት እንደሚደግፉ ማማከር፡፡

2. <u>የአልኮል እና የሌላ ድረግ (AOD) ትምህርት ሴሚናር፤</u> በዝቅተኛ ደረጃ ያሉ ያለአግባብ ድረግ አጠቃቀም ችግር ላለባቸው ተማሪዎች እና ወላጆችን ለመደገፍ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አማራጭ መንገዶች ይሰጣል፡፡ ተማሪዎች እና ወላጆችን/አሳዳጊዎች ለመደገፍ ከተማሪ የድራግ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የአደጋ ምልክቶችና እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በሚሰጠው ወርሃዊ ሴሚናር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ ፡፡

3. <u>በቅድሚያ በትምህርት ጣልቃ መግባት ስብሰባዎች፤</u> ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የእፅ አለአግባብ መጠቀም ጣልቃ መግባት በተከታታይ የሚካሄዱ ስለ ድራግ ምክንያትና ውጤት የሚያስረዱ ተማሪዎችን ለማስተማር የድራግ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ችግሮች ትምህርት የሚሰጥባቸው ስብሰባዎች ናቸው ፡፡ በቅድሚያ ጣልቃ መግባት የሚያተኩረው እጩ ተማሪዎች በመርዳት ከድራግ አጠቃቀም ወይም ማሳራጨት ጋር በተያያዘ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የባህሪ ህግ መጣስ እንዲረዱ የማድረግ ሂደት ላይ ነው፡፡ የSAC የይዘቱን እና በእያንዳንዱ ሁኔታ የትምህርት ስብሰባ ምን ያህል ሰዓት እንዲሚካሄድ ይወስናል፡፡ ህክምና በዚህ ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ አገልግሎቶች ውስጥ አይካተትም፡፡

4. <u>የታቀደ የታለመ ጉዳይ አመራር፤</u> ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አጭር ጊዜ የታቀደ የጉዳይ አመራር አገልግሎት ተማሪዎችን ፍላጎት ከአገልግሎቶች ጋር የማገናኘት በተለይ በሰለጠኑ በማህበረሰቡ ውስጥ ወደ አሉ ባለሞያዎች (የውጭ አገልግሎት ሰጪዎች) ሪፈራል የመላክ ስራ ያከናውናል፡፡ አጭር ጊዜ የታቀደ የጉዳይ አመራር የሚያካትተው መቆጣጠርን እና መልሶ መግባት የሚመለከቱ ጉዳዮችን ማማከርን ያጠቃልላል፡፡ ተማሪው ቴራፒስት ባለሞያ ካለው እና ህክምና በመከታተል ላይ ከሆነ አገልግሎት በመቆጣጠር እና በመስጠት ላይ ላለው ህክምና ድጋፍ መስጠት እና በወላጅ/አሳዳጊ ፍቃድ ከወቅቱ አገልግሎት ሰጪ ጋር መተባበር ፡፡

D. **የመዝገብ ሪከርድ አያያዝ፤** ሚስጢራዊነት መጠበቅ ወሳኝ በሆነ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አለአግባብ ድራግ አጠቃቀም መከላከልና እና ጣልቃ መግባት ፕሮግራም ወሳን ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎች የራሳቸውን ሚስጢር የማስጠበቅ መብት አላቸው እና ከስም መነሳት ማንነታቸው የተጠበቁ መሆኑን ሊሰማቸው ይገባል ህክምናውን ለማቆረጥ ምክያንት ሊሆን ስለሚችል፡፡ ነገር ግን ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ተቋማት እንደ የኮሚዩኒቲ አገልግሎት ቦርድ(CSB) ወይም የልጆች እና የሰው አገልግሎቶች ዲፖርትሜንት(DCHS) በመደበኛነት መረጃ ከዚህ ምርመራ ውትና የህክምና ተሳትፎ በተመለከተ ሪከርድ መያዝ አለበት የቤተሰብ ትምህርት መብቶችና የፕራይቬሲ ፖሊሲ(FERPA) 42 CFR Part 2 (የእፅ አለአግባብ መጠቀም ችግር የህመምተኛ ሪከርድ ) እና የጤና ኢንሹራንስ ተላላፊነት እና ተጠያቂነት ህግ (Health Insurance Portability and Accountability Act) (HIPAA) እና ተዛማጅ ደንቦች፡፡

## V. ሚስጥራዊነት

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተማሪዎችን ታሪክ ሚስጢራዊነት ያስጠብቃል እና ቅድሚያ ይሰጣል። የመረጃ ማሰራጨት በFERPA, 42 CFR Part 2, HIPAA እና ተዛማጅ ደንቦች መሰረት የሚከናወን ይሆናል ።

ሚስጢራዊነት አሰራር በተመለከተ በፌደራል የሚታገዝ ፕሮግራም ለሚከታተሉ እፅ አለአግባብ የመጠቀም ፕሮግራም 42 CFR Part 2 የሚወስን ነው ይህም ፤

- ለማንኛውም ፕሮግራም ወይም ያለአግባብ እፅ የመጠቀም ትምህርት አሰጣጥ፣ ሕክምና እና ወይም መከላከል ላይ የተሳተፈ ግለሰብ ይመለከተዋል። ማንኛውም ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ያለአግባብ እፅ መጠቀም የመለየት ስራ የሚከናወን ባለሞያ ፣ በጣልቃ ገብነት ትምህርት ወይም ሪፈራል ለህክምና የመስጠት አገልግሎት ማንነት የሚያሳዮ መረጃዎች፣ የምርመራ ውጤት ፣ ወይም ህክምና የማንኛውም ተማሪ ያለአግባብ እፅ የመጠቀም ፕሮግራም የሚያገኝ ተማሪን ማንነት ያለ ተገቢ ፈቃድ ማሳወቅ አይቻልም።
- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ባለሞያዎች ያለአግባብ እፅ መጠቀም ጋር የተገናኙ መረጃዋችን ለማሰራጨት ከፈለጉ የፅሁፍ ፈቃድ በወላጅ/አሳዳጊ ወይም ከ14 አድሜ ባላይ ከሆኑ በተማሪው ፈቃድ ማግኘት አለበት። እንዲሁም እነዚያ ድርጅቶች ከተማሪው ጋር ያለአግባብ እፅ መጠቀም ጋር በተያያዘ አገልግሎት የመስጠት ግንኙነት የሚኖራቸው ከሆነ መረጃ መልቀቁ ሊፈፀም ይችላል። እኒዚህ መረጃዋች የተሰራጪባቸውን ተቋማት ዝርዝር ፍላጎት ተማሪው እና የወላጅ/አሳዳጊ ሊያውቁ ይገባል
- ከእፅ ያለአግባብ መጠቀም ትምህርት፣ ሕክምና እና/ወይም መከላከል ጋር የተያያዘ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እንደገና እንዲያሳውቅ አይፈቀድም (ያለ ግልፅ ፅሁፍ ስምምነት) ። ጥቅል የመረጃ ስርጭት አይፈቀድም።
- የሚጠበቅ መረጃ የግድ መገልፅ ላለበት ለስቴት የልጅ- ጉዳት-እና-ችላ ማለት ሪፖርት የሚያስገድድ ከሆነ፣ ከእፅ አለአግባብ አጠቃቀም ጋር የተያያዘ የሞት ምክንያት ሪፖርት የተደረገ ከሆነ ወይም እንዲገልፅ በፍርድ ቤት የተጠየቀ ከሆነ የመረጃ ስርጭት ይፈቅዳል።
- የተማሪውን ማንነት መለያ መረጃዋች የመግለፅ ፈቃድ በተለየ ሁኔታ ከመድሃኒት አሰጣጥ የድንገተኛ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጥ ይፈቅዳል።

የፀደቀው፤ ዲሴምበር 20፣ 2018

የሕግ ማጣቅሻ፤ 20 U.S.C. §§1415(k)(1)(G)(ii), 1415(k)(7)(A), 1415(k)(7)(B).
21 U.S.C. §§ 812.

42 U.S.C. §§ 2.122.51
45 C.F.R. §§ 164.502, 164.506(c), 164.512(f).

የቨርጅኒያ ህግ 1950 እንደተሻሻለው §§ 16.1-305.1, 18.2-247, 18.2-250, 18.2-250.1, 18.2-255.2, 22.1-78, 22.1-276.01, 22.1-277.08.

8 VAC 20-81-10.

የቃላት መፍቻ፤ CLA የደንብ መተላለፍ እና ያለአግባብ እፅ መጠቀም ሪፖርት
IGAG ስለ ድራግ ፣ አልኮል እና ሲጋራ ማስተማር
JFC የተማሪ ባህሪ
JFC-R የተማሪ ባህሪ መመዘኛ ደረጃ
JFCF -R/JFCI-R የአልኮል እና ሌሎች እፃች ድራጎች(AOD ) አለአግባብ መጠቀም፤
JGD/JGE የተማሪ እገዳ/መባረር
JGD-R/JGE-R የተማሪ እገዳ/መባረር ደንቦች
JGDA የአካል ጉዳት ያለው ተማሪ የሥነ ሥርዓት ቅጣት

JHCD ለተማሪዎች የመድሐኒት አሰጣጥ አሰራር
JHCD-R ለተማሪዎች የመድሐኒት አሰጣጥ አሰራር ደንቦች
JHG ልጅ የማንገላታት እና በግዴለሽነት አለመጠበቅ ሪፖርት
JO የተማሪ ሪከርድ ማህደር